# ኮሽ ሲል ፌደራሊዝም የጥላቻ ዘመቻ

*ክሩቤል ሚሃጻደቅ 10-03-17*

ከሰሞኑ ሀገራችን እየተከተለችው ባለው የዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ስርዓት ላይ የተለያዩ ኃሳቦች በማነዘር ላይ ናቸው፡፡ በአንድ በኩል ስርዓቱን የሚያብጠለጥሉ ኃይሎች ብቅ ብቅ እያሉ ነው፡፡ በተለይም በፖለቲካ ፓርቲና በጋዜጠኝነት ስም የታቀፉ አንዳንድ ወገኖች በስርዓቱ ላይ <<ድሮም ብለን ነበር>> የሚል ይዘት ያላቸው ሚዲያዎች በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል የፌደራሊዝም ስርዓቱ ግጭቶችንና ቅራኔዎችን አስወግዶ ሀገሪቱ ሁለንተናዊና ፈጣን ለውጥ እንድታስመዘግብ ያስቻለ ፍቱን መድሃኒት እንጂ የግጭት መንስኤ እንዳልሆነ የሚከራከሩ ወገኖች በርካቶች ናቸው፡፡

ስርዓቱን የሚዣቹ አካላት በአንዳንድ አካባቢዎች አልፎ አልፎ ግጭቶች መከሰታቸውንና በተለይም በቅርቡ በኦሮሚያ እና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ያጋጠመውን ወቅታዊ ችግር አስረጅ አድርገው በማቅረብ ብዙ ጽፈዋል፤ ብዙ ብለዋል፡፡ እውን ኢትዮጵያ የምትከተለው ፌደራሊዝም ስርዓት የግጭት መንስኤ ወይስ ግጭቶችንና ቅራኔዎችን ያስወገደ ስርአት ነው? የሚለውን በማስረጃ አስደግፎ ሚዛናዊ አቋም ማያዝ ይገባልና ትንሽ ልበል፡፡

ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፌደራሊዝም መከተል ከጀመረች ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል፡፡ በኢትዮጵያ የፌደራሊዝም ስርዓት ለመከተል ተጨባጭ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ ባለፉት ስርአቶች በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ በነበረው የመደብና የብሄር ጭቆና የተለያዩ ቅራኔዎችን ፈጥሮ ሀገሪቱን ለእርበርስ ግጭቶች ዳርጓት ቆይቷል፡፡ በተለያዩ አከባቢዎች የሚገኙ ህዝቦችም የብሔር መብት እንዲከበር በርካታ ጥያቄዎች ሲያነሱ እንደነበርም ይታወቃል፡፡ በ1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት የብሄር መብት ከ<<መሬት ላራሹ<< ቀጥሎ ዋነኛው ጥያቄ እንደነበረም የሚታወስ ነው፡፡

ከ1983 ዓም በፊት በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል፣ ኢትዮጵያ ሶማሌ፣ በዓፋር ወዘተ አካባቢዎች ብሄርን ማስረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎች ነበሩ፡፡ ይህም ለዘመናት ሚለስ አጥቶ የቆየውን የብሄር ጥያቄ ወደ አላስፈላጊ ግጭት አምርቶ እንደነበር ማንዘብ ይቻላል፡፡ ኢህአዴግ ስልጣን ሲይዝ 17 የሚጠጉ ብሄርን ማስረት አድርገው የተማሰረቱና የማንጠል ጥያቄ የሚያነሱ ኃይሎች መኖራቸው በወቅቱ የሀገራችን አንድነት ምን ያህል በአደገኛ ሁኔታ ወስጥ እንደነበር ማንዘብ ይቻላል፡፡

በወቅቱ ኢትዮጵያ ለብተና ዳርጓት የነበረውን በጭቆና ላይ የተማሰረተው የአሃዳዊ የመንግስት አወቃቀር ማስቀጠል የሚይታሰብ ነበርና ሁሉም ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች አንድነታቸውን ጠብቀው እንዲቀጥሉ የሚያስችል አዲስ አወቃቀር መከትል አማራጭ ያልነበረው ጉዳይ ነበር፡፡ እናም ለማንጠል አኮብኩበው የነበሩ ኃይሎችን ጨምሮ ለዘመናት የቀጠለውን የህዝቦች ጥያቄ ሚልስ ለማስጠት ህገመንግስታዊ የፌደራሊዝም

ስርዓት ሁነኛ መፍትሄ ሆነ። ብሄሮች ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች አንድነታቸውን የሚያጠናክርና አብሮ የመኖራቸው ዋስትና የሆነውን ህገ መንግስት ማርቀቅ ግድ ይል ነበር። በዚህም ከ28 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ወይይት አድርጎ የተግባበት የኢፌዴሪ ህገ መንግስት ህዳር 29ቀን 1987 ዓም ሊጸድቅ ቻለ።

በህገ መንግስቱ መሰረት የፌደራል ስርዓቱ ተግባራዊ ሲደረግ በተለይም ባለፈው ስርዓት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች የነበሩ እና ሌሎች ኃይሎች <<ነጻ ፕሬስ>> በሚል ሽፋን ይዘጋጁ በነበሩ ጋዜጦችና መጽሄቶች እንዲሁም ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ስርዓቱን ከፉኛ በመኮነን የፌደራል ስርዓቱ ሀገሪቱን በአጭር ጊዜ ለብተና እንደሚዳርጋት አሟረቱ። የትምክህት ኃይሉ በህገ መንግስቱ መሰረት የተደረገውን የፌደራሊዝም አወቃቀር ለማውዓዝ የቀደመው አልነበረም። ያለፈውን ስርዓት እንከን አልባ አድርጎ በማስበክ አዲሱን አወቃቀር አወገዘ። ትናንት ህዝብን ሲጨፈጭፉ የነበሩ ኃይሎች እነርሱ የተከተሉት የተሳሳተ አካሄድ ሀገሪቱን ለብተና ዳርገዋት እንደነበር ከደው ገና በለጋ ዕድሜ ላይ የሚገኘውን ስርዓት ማብጠልጠላቸውን ቀጠሉ።

የጥበት ኃይሎችም ቢሆን ስርዓቱን ከማብጠልጠል አልተቆጠቡም። በአዲሱ የፌደራል ስርዓት የተገኙ ትሩፋቶችን በመካድ ባለፉት ስርዓቶች የነበረውን ጭቆና ዛሬም እንደቀጠለ አድርገው በማቅረብ ስርዓቱን ማጥላላት ተያያዙት።

በአገራችን እውን የሆነ የፌደራሊዝም ስርዓት በተለያዩ አካባቢዎች ሲነሱ የነበሩ የመንጠል ጥያቄዎችን እንዲከስሙ በማድረግ አዳንዶች እንዳሟረቱበት ሳይሆን በተቃራኒው የአንድነታችን መሰረት ሆነ። ዛሬም ድረስ እንዳንድ ኃይሎች በስርዓቱ የተጎናፀፍነውን ድል በመካድ የማጥላላት ዘመቻቸውን በመቀጠል፤ በአዲስቷ ኢትዮጵያ የተመዘገቡ በዓይን የሚታዩ በእጅ የሚዳሰሱ አመርቂ ድሎችን በመካድ ከብዙሃኑ ህዝብ በተቃራኒ ሲቆሙ ይታያል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ በፈጣን ሁለንተናዊ ለውጥ ውስጥ የመገኘቷ ምስጢር የተከተለችው የፌደራሊዝም ስርዓት ብሄር ብሄረሰቦችና ህዘቦች በአገራቸው ላይ በነፃነት የመስራት ሃብት የማፍራትና አገራቸውን የመለወጥ ነፃነት በማጎናፀፋቸው ነው። በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ባለፉት ስርዓቶች ውስጥ በደረሰባቸው ጭቆና ምክንያት ኢትዮጵያዊነታቸውን እንዲጠሉ ሆነው የነበሩ ብሄር፣ ብሄሮችና ብሄረሰቦች መብታቸውን በህገ መንግስታዊ መንገድ ሳይሸራረፍ እንዲከበር በማድረጉ ለሀገራዊ አንድነታቸው ጠበቃ የሚቆሙ ሆነዋል። ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ከመጎናጸፋቸው በላይ በፌደራል ደረጃም እኩልና ተመጣጣኝ ውክልና ማግኘት ችለዋል። በዚህ ሂደት ቋንቋቸው፣ ባህላቸውንና ሌሎች እሴቶቻቸውን የሚያሳድጉበት መብት ተጎናጽፈዋል። አካባያቸውን እንዲያለሙ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል።

እንደ ሀገር ሲታይ በየዓመቱ ፈጣን እድገት ከሚያስመዘግቡ ሀገሮች ተርታ ማሰለፍ የምትችል ተስፋ ያላት ሀገር መፍጠር የተቻለው በዚህ የዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ስርዓት ነው፡፡ ባለፉት 13 ዓመታት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በ10ነጥብ5 በመቶ ማደግ ተችሏል፡፡ እድገቱ በየደረጃው ያሉ የህብረሰተብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ያደረገ እንደሆነ የነፍስ ወከፍ አማካይ ገቢ በማስደግና እና ደህነትን በመቀነስ የተጫወተውን ሚና ማየት ይቻላል፡፡ ከ12 ዓመታት በፊት ከፍጹም ደህነት ወለል በታች ይኖር የነበረው ህዝብ 38ነጥብ7 በመቶ ሲሆን በ2009 ዓም ሚጨረሻ ወደ 23 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአማካይ የ13ነጥብ8 በመቶ ዕድገት በማስመዘገብ በ2002 ዓም ከነበረበት የ373 የአሜሪካን ዶላር በ2008 በዓም ወደ 794 አሜሪካን ዶላር ከፍ ብሏል፡፡

ፈጣን ዕድገቱ የዜጎችን ኑሮ ከማሻሻሉ በተጨማሪ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚከሰተውን ድርቅ የከፋ ጉዳት ሳያደርስ በራስ አቅም ለመካላከል አስችሏል፡፡ በ2007/08 ዓም በ30 ዓመታት ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ከባድ ድርቅ አጋጥሞ የነበረ ቢሆንም በሀገረቱ ለበርካታ ዓመታት የተመዘገበው ፈጣንና ተከታታይነት ያለው ዕድገት ድርቁን መቋቋም ኢንዲቻል አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሚኩ በ2009 ዓም ያጋጠመው ድርቅ በተመሳሳይ ሁኔታ መቋቋም ተችሏ፡፡ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት በድርቅ ምክንያት ዜጎች እንደ ቅጠል ይረግፉባት የነበረችውን ሀገር ዛሬ የሚከሰተውን ድርቅ በሰዎች ብቻም ሳይሆን በእንሳሳት ላይም የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ የሚያደርግቅ አቅም ተፈጥሯል፡፡

በማሰረተ ልማት ማስከ በመንገድ፣ በባቡር፣ በአየር ትራንስርት እንዲሁም በቴሌኮም ማስኮች አመርቂ ስኬት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ የትራንስፖርት ማስፋፋት ደግሞ የሰዎችን ሁለንተናዊ ግንኙነት በማቀላጠፍ ፈጣን ልማቱን ይበልጥ እንዲጠናከር አስችሏል፡፡ በኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ ለማድረግ የተከናወኑ ስራዎችም በተመሳሳይ ሚኩ አንጸባራቂ ስኬቶች ተመዝብዋል፡፡ የሀገሪቱን የኃይል አቅርቦት በብዙ እጥፍ ማስደግ የተቻለ ሲሆን ሀገራች እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች በራሷ አቅም መገንባት ጀምራለች፡፡ ትናንት በድንቁርና እና በረሃብ ትታወቅ የነበረችው ሀገር ያንን አስከፊ ዘመን ተሻግራ አኩሪ የልማት ስራዎችን በማከናወን ላይ ትገኛለች፡፡

በማህበራዊ ልማት በጤና በትምህርት፣ እንዲሁም በውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ኢትዮጵያ ለዓለም አርአያ የሆኑ ከፍተኛ ስኬቶች የተመዘገበባቸው ማስኮች ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱ አመርቂ ስኬቶች የተመዘገቡት ደግሞ በዋናነት በሀገራችን አስተማማኝ ሰላም በማስፈኑ ነው፡፡ የአስተማማኙ ሰላም ማስፈን ምንጭ ደግሞ በህዝቦች ሚፈቃቀድ የተማሰረተው ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ስርዓት ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በማንኛውንም የዕድገት ሂደትና ጉዞ ሚልካም አጋጣሚዎች እንዳሉ ሁሉ ተግዳሮቶችም አሉ፡፡ በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረውን የማብታተን አደጋ ያስቀረው የፌደራሊዝም ስርዓት በርካታ ችግሮች እየፈታ እዚህ የደረሰ ሲሆን እንደማንኛውም በመገንባት ላይ ያለ ስርዓት ተግዳሮቶችና ፈተናዎች ሊያጋጥሙት እንደሚቹሉ እሙን ነው፡፡ ዋናው ጉዳይ ችግሮች የሚፈታበት አገባብ ምን መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ በአንድ በኩል ማንኛውንም ውሳኔዎች የህዝቡን ፍላጎት ማእከል ያደረጉ እንዲሆኑ ማድረግ ሲሆን ችግሮቹ በሕገ መንግስቱ ማስረት መፍትሄ ማስጠትም ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡

አልፎ አልፎ እያጋጠሙ ያሉ ግጭቶች መከሰት ያልነበረባቸው፤ ዳግም እንዳይከሰቱ ተገቢውን ትምህርት መውሰድ አስፈላጊ ቢሆንም ችግሮቹ በማንኛውም ታዳጊ ስርዓት ሊያጋጥሙ የሚቹሉ ናቸው፡፡ ከወሰን እና ከማንነት ጋር ተያይዞው የሚነሱ ጥያቄዎች ከፌደራል ስርዓቱ ጋር በማያያዝ የሚደረገው ዘመቻ ሌላ ተልዕኮ ያለው ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በቅድመ 1983 ዓም በሁሉም አካባቢዎች የነበሩ ግጭቶች እና ቅራኔዎች ስፍር ቁጥር አልነበራቸውም፡፡ ሁሌም ነገሮችን በሚዛናዊ ዕይታ ማየት የተሳናቸው ኃይሎች ሶስት ነገሮች ማየት አይፈልጉም ወይም ይዘናገሉ፡፡ አንደኛው ከ1983 ዓም በፊት በየአካባቢው የነበሩ ግጭቶችን ይክዳሉ፡፡ ሀገሪቱን ለብተና ዳርጓት የነበረውን ጨቋኝ አሃዳዊ ስርዓት በማንቆለጳጰስ ትናንት በህዝቦች ላይ የደረሰውን በደል ማንሳት አይፈልጉም፡፡ ሁለተኛዉ የፌደራል ስርዓቱ ያስገኛቸውን ሚልካም ስኬቶች በማጥላላት አልፎ አልፎ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ብቻ በማጉላትና በማውገርገር ላይ የተጠመዱ ናቸው፡፡ በጋዜጠኝነት፣ በፖለቲካ ድርጅትና በሌላ ተቋም ስም ተከልለው ስርዓቱን ሲያጥላሉ ወለው ያመሻሉ፡፡ በሶስተኛ ደረጃ እነዚህ ሁሉንም ነገር ማጥላላት ላይ የተጠመዱ ኃይሎች ይህን ስርዓት ከመተቸት የዘለለ አማራጭ የመንግስት አወቃቀር ሲያቀርቡ አይታዩም፡፡ በማስረቱ ኢትዮጵያ የአሃዳዊ የመንግስት አወቃቀር ምን ያህል ወደ ማስቀለኛ መንገድ አስገብቷት እንደነበር የሚታወቅ ስለሆነ ከፌደራል ስርዓት ውጭ ምንም ዓይነት አማራጭ ሊያቀርቡ አይችሉም፡

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች በሚፈቃቀድ ላይ የማስረቱት ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ስርዓት እኩል የሚልማትና አንድነታቸውን የማጠናከር ዕድል አጎናጽፏቸዋል፡፡ እናም ስርዓቱ ገና አዳጊ ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚያጋጥሙ አንዳንድ ችግሮች ለቀጣይ ትምህርት የሚሆኑ ስርዓቱንም የሚያጠናክሩ ናቸው እንጂ የመጣንበትን መንገድ አስትተው ወደኋላ የሚቀለብሱ አይደሉም፡፡ እናም ኮሽ ባለ ቁጥር የችግሩን መንስኤ በአግባቡ አይቶ ምክንያታዊ ሃሳብ ከማስንዘር ይልቅ በጭፍን ጥላቻ የፌደራል ስርዓቱ ላይ የሚደረገው ዘመቻ እውነታው በብዙሃኑ ህዝብ ዘንድ ያለ በመሆኑ ትዝብት ውስጥ ከማከተት ባለፈ ፋይዳ የሌለውና ቀደም ባሉ ዓመታት የትምክህትና የጥበት ኃይሎች በስርዓቱ ሲያደረጉት የነበረውን የማጥላላት ዘመቻ ለማጠናከር የማቀርብ መሆኑ የሚረጋግጥ ነው፡፡ የፌደራል ስርዓቱና የአብሮነት ዋስትና የሁሉም የለወጥ ጉዞዎች ምንጭ እንጂ የግጭት መንስኤ አይደለም፡